# Arlington Public Schools (አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች)

የትምህርት መምሪያ

---

ውድ ወላጅ፣

*የንግግር ችሎታ ፍተሻ/ምርመራ (Phonological Awareness Literacy Screening)* (PALS-K) ለልጅዎ ተደርጎ ነበር። PALS -K በመላው የቨርጂኒያ አካባቢ ሥራ ላይ የዋለ መደበኛ የምርመራ ዝርዝር ነው። አስተማሪዎች የሚያስተምሩትን ትምህርት ለማዘጋጀት የሚረዳ መረጃ ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የ PALS ግምገማ ለሁሉም አንባቢዎች ተገቢ ትምህርት ለማዘጋጀት የሚረዳ ዕቅድ ለማቀድ ለአስተማሪዎች ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል።

ፍተሻው ከድምጽ እና ከጽሑፍ እውቀት ጋር የተያያዙ በርካታ ተግባራትን ያካትታል። በተለይም የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያጠናቅቁ ተማሪዎች ተጠይቀዋል። እያንዳንዱ ተግባር በክፍል-ደረጃ የሚጠበቁ ውጤቶች አሉት፤ እንዲሁም **አጠቃላይ የተደመረ ውጤት** ለመፍጠር የተመረጡ ተግባራት ታክለዋል።

**PALS--K ተግባራት:**

- **የድምጽ አወጣጥ ግንዛቤ** - ከሶስት ስዕሎች ስብስብ ውስጥ ከሚያዩት ምስል ጋር የሚዛመደው የትኛው እንደሆነ እንዲለዩ ይጠየቃሉ።
- **የመጀመሪያ ድምጽ ግንዛቤ** - ከሶስት ስዕሎች ስብስብ ውስጥ ከሚያዩት ምስል ጋር የሚዛመደው የትኛው እንደሆነ እንዲለዩ ይጠየቃሉ።
- **የፊደል እውቀት** - ተማሪዎች 26 ንዑስ ፊደላት (lower-case letters) እንዲጠሩ ይጠየቃሉ።
- **የፊደል ድምጾች** - ተማሪዎች 26 ንዑስ ፊደላት (lower-case letters) እንዲጠሩ እንዲሁም ሶስት ዲግራፎችን (digraphs)፣ እንደ /sh/ የመሳሰሉ አንድ ላይ ሲነበቡ አንድ ድምጽ የሚሰጡ ሁለት ፊደሎችን ድምጾች እንዲያወጡ ይጠየቃሉ።
- **የፊደል አደራደር (Spelling)** - ተማሪዎች አምስት ተነባቢ-አናባቢ-ተነባቢ ቃላትን ለምሳሌ /t-o-p/ የሚጽፉ ሲሆን cat ለመጻፍ /k-a-t/ ብለው መጻፍን የመሳሰሉ በድምጽ አንድ አይነት የሆኑ ፊደሎችን አቀያይረው ቢጽፉም ውጤት ያገኛሉ።
- **ቃላትን ለይቶ ማወቅ** - ቃላትን ለይቶ ማወቅ PALS-K በምርጫ የሚሰራ ቢሆንም የተወሰነ የማንበብ ችሎተ ላላቸው ተማሪዎች ሊሰጥ ይችላል። ፕሪፕራይመር (Preprimer)፣ ፕራይመር (Primer) እና አንደኛ ክፍል ደረጃ ዝርዝሮች ቀርበዋል።

አጠቃላይ ማነጻጸሪያዎች በፎልና ስፕሪንግ ላይ እንዲደረጉ ተወስነዋል፣ እንዲሁም የንዑስ ፈተና ማነጻጸሪያዎች**።** አጠቃላይ ማነጻጸሪያው ወይም አጠቃላይ ድምር ነጥቡ ተብሎ የሚጠራው ተማሪው *በሚጠበቀው ደረጃ ላይ፣ በታች ወይም ሚጠበቀው የክፍል ደረጃ በላይ* መሆኑን ያመለክታል። የንዑስ ፈተና ማነጻጸሪያዎች የተወሰነ ክህሎት ላይ የክፍል ደረጃ አፈፃፀምን ያመለክታሉ። አስተማሪዎች ተገቢ የንባብ እና የፊደል ትምህርት ለማቅረብ ከፍተሻው የተርገኘውን መረጃ ይጠቀማሉ። *የመግቢያ ደረጃውን* (Entry Level) ማነጻጸሪያ ያላሟሉ ተማሪዎች በ PALS ላይ እንደተመከተው የተወሰኑ ክህሎቶች ላይ **ተጨማሪ** ትምህርታዊ ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

ስለቀጣይ ድጋፍዎ እናመሰግናለን።